


# በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣

## ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ

# ከኦክቶበር 1-31/2025 የነበረው የአየር ጠባይ ግምገማ እና

# ከኖቬምበር 1-30/2025 የሚኖረው የአየር ጠባይ ትንበያ እና

# ምክረ ሃሳብ

ኖቬምበር 2025

አዲስ አበባ

ስልክ+251115538394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et


# በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣
# ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ

## 1. እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ 31/2025 የነበረው የአየር ጠባይ

ባለፈው የኦክቶበር ወር ለበጋ ዝናብ መፈጠር ምቹ የሆኑ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ከቀን ወደ ቀን እየተስፋፉ ከመምጣታቸዉ ጋር ተያይዞ፤ በተለይም በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸዉ በሁኑት የደቡብ አጋማሽ የሀገሪቱ ስፍራዎች ላይ እንዲሁም በክረምት ወቅት ዝናብ ሲያገኙ የነበሩት የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ የተሻላ ገጽታ ነበራቸዉ፡፡ በመሆኑም፤ በዚህ ወቅት በመደበኛ ሁኔታ ዝናብ የሚያገኙት የደቡብ ኦሮሚያ ዞኖች፣ የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ደቡባዊ ዞኖች፣ የደቡብ እና የደቡብ ምስራቅ ሶማሌ ዞኖች ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ የተመዘገበ ሲሆን፤ አልፎ አልፎ ጠንከር ያለ የደመና ክምችት ተስተውሎባቸዋል። በተጨማሪም በአንዳንድ አካባቢዎችም በፀሀይ ኃይል ታግዞ ከተፈጠረው ጠንካራና ዝናብ ሰጪ ደመናዎች ጋር ተያይዞ በ24 ሰዓት ውስጥ ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቧል። በተጨማሪም በ24 ሰዓት ዉስጥ ከ30 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ከተመዘገበባቸው የሚቲዎሮሎጂ ጣቢያዎች መካከል አርባ ምንጭ 23.4፣ 23.3፣ 41.7፣ ጎሬ 55.6፣ 32.4፣ 29.2፣ 21.4፣ 26.7፣ 31.9፣ ባህር ዳር 35.2፣ 46.2፣ 33.8፣ ነገሌ 13.6፣ 22.3፣ 34.5፣ ሮቤ 17.2፣ አቦቦ 20.6፣ 37.4፣ አማን 56.6፣ ነቀምት 25.4፣ 26.2፣ አዲስ አበባ ጥቁር አንበሳ 23.4፣ አዲግራት 20.8፣ አይራ 22.2፣ አቦምሳ 25፣ አልጌ 25፣ 23.5፣ 35፣ 40፣ አማን 24.3፣ አንገር ጉትን 20፣ 20.6፣ አርጆ 24.6፣ 28.8፣ 20.2፣ 41.4፣ 26.8፣ 18.6፣ 22፣ አየሁ 31.8፣ 21፣ አይከል 28.2፣ አሶሳ 34.7፣ በደሌ 20.2፣ ቦሬ 36፣ 46.2፣ 22.7፣ 22.3፣ 23.4፣ ቡለን 27፣ 20.2፣ 38.4፣ 20፣ 20.8፣ 38.2. 38.2፣ 32.2፣ 21፣ ቡሬ 41፣ 70.7፣ 25.5፣ ቡራ 28.1፣ 28.8፣ 60.5፣ ቡርጂ 27.6፣ ቻግኒ 25.4፣ 30.5፣ 24.6፣ 22.8፣17፣ ጨዋቃ 22፣ 28፣ 25፣ 24.4፣ 16፣ 30፣ 6.4፣ ጭራ 23.4፣ 21፣ዳንግላ 20.4፣ ደምቢ ዶሎ 23.8፣ 23.5፣ 18፣ ዲላ 35፣ ዶሎመና 20.7፣ 20.4፣ 20.3፣ 30.3፣ 30.4፣ ኢጃጂ 47.7፣ ፉኙዶ 25፣ 20.6፣ 22.8፣ 25.5፣ ጋምቤላ 51.8፣ 26.7፣ ጋቲራ 20.2፣ 20.8፣ ጊዳ አያና 21.6፣ 17.3፣ 22.9፣ ጊምቢ 25.5፣ 23.1፣ 27.7፣ ጎሎልቻ 20፣ ቡሌ ሆራ 26፣ 21፣ 25.2፣ 40፣ ጃራ 20፣ 25.6፣ 25.7፣ ላሬ 31.4፣ ጂንካ 24.2፣ 15.1፣ 37.7፣ ካቺሴ 35.5፣ ቀብሪ ዳሀር 24.4፣ ላይብር 26፣ 27.7፣ ሊሙገነት 57.5፣ 42.7፣ 39.4፣ ቀብሪ ዳሃር 15.3፣ ማጂ 24፣ 31፣ 25፣ 18.8፣ ማሻ 90.2፣ 20.5፣ ምዕራብ አባያ 37፣ ሞያሌ 23.4፣ ነጆ 34.4፣ 24.2፣ 34.5፣ ሻምቡ 35.8፣ ሽሬ 29.5፣ 38.4፣ ሲሪንቃ 26.2፣ ፓዌ 38.5፣ ሳዉላ 28.7፣ 31.2፣ ሻሁራ 16.1፣ ሽሬ 15.9፣ ተርጫ 22.9፣ 28.8፣ 42፣ ቴፒ 54.8፣ ወራቤ 21.8፣ ያቤሎ 34.6፣ 43.2፣ 23.4፣ 24.3፣ አቦ ሞሪንጋ 29.2፣ 22.2፣ 52፣ አጋሮ 22.5፣ 22፣ 33፣ 18፣ አንጋጫ 24.5፣ 23.5፣ አሺ 25.5፣ 15.4፣ አሸሪ 23.4፣ አታንጎ 25፣ 28.7፣ 49፣ 21.5፣ 46.5፣

በቆጂ 22.3፣ ቢላምቢሎ 23.4፣ 23.3፣ 22.7፣ 33፣ 22.2፣ 44.6፣ 36፣ ቡልቂ 22.4፣ 25.9፣ 19.4፣ 25.1፣ ቦርቃ 24.6፣ 42.3፣ ቡሬ 22፣ ዳራማሎ 20.1፣ ፎጉ ሌቃ 20፣ ጉበይሬ 75.6፣ ጌጫ 17፣ 19፣ ጉበቲ 22.7፣ 34.7፣ 33.9፣ 33.6፣ 21፣ 24.1፣ ሃሮ 30.2፣ ሀመሮ 20.7፣ ሀንቲ 31.4፣ ቅዳሜ ገበያ 26.8፣ 27.6፣ 48.8፣ 22.4፣ 37.6፣ 58.6፣ 59.8፣ 48.6፣ 56.7፣ 46.3፣ 59.8፣ 26.6፣ 37.8፣ 28.9፣ 47.8፣ 28.4፣ ኮበን 33፣ ኩሚ 21.1፣22.5፣ መካነ ኢየሱስ 23.8፣ መርጦ ለማሪያም 23.3፣ ሙጊ 26.9፣ ኦንጋ 43.3፣ 26.5፣ 42.6፣ 28.3፣ 29.6፣ 28.8፣ ሲቦ 18.4፣ 15.7፣ ሸንዲ 22.5፣ ሸቤ 20.5፣ ተርቆዲ 23.7፣ 36.8፣ ትንሹ ሜጢ 31.3፣ 36.8፣ 28.6፣ 25.6፣ መንደር አስራ ሶስት 20.2፣ 20.4፣ መንደር አስራ አንድ 46፣ 53.5፣ 96፣ መንደር ሰባት 35.7፤ያንፋ 40.3፣ 30.3፣ 37.8፣ 30.3፣ 28.2፣ 37.8፣ 28.3፣ 38.4፣ 48.2፣ 22.3፣ 30.3፣ 43.5 ያዮ 21.7፣ 24.6፣ 42.5፣ 20.4፣ ዩና 24.9፣ ይርጋጨፌ 20.4፣ እንዲሁም ይርጋለም 28.6 ሚ.ሜ የሚደርስ ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቦባቸዋል።

በአጠቃላይ ባለፉዉ ወር በሃምሳ ስምንት (58) የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ በ24 ሠዓት ዉስጥ ከ30 ሚ.ሜ በላይ የሆነ ከባድ መጠን ያለዉ የዝናብ መጠን ነበራቸዉ (ምስል 1)፡፡ በተጨማሪም ቢጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታች በሁኑት የደቡብ አጋማሽ የሀገሪቱ አከባቢዎች እንዲሁም በአንዳንድ የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑ የምዕራብና የደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ በ24 ሰዓት ዉስጥ 40.0 - 96 ሚ.ሜ የሚደርስ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ ከ50 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ከተመዘገበባቸው የሀገሪቱ አከባቢዎች መካከል መንደር አስራ አንድ፣ ማሻ፣ ነቀምት፣ ጉበይሬ፣ ቡሬ፣ ያቤሎ፣ ቅዳሜ ገበያ፣ ሊሙገነት፣ ጎሬ፣ ቴፒ፣ አማን፣ ደበረ ሲና፣ አቦ ሞሪንጋ፣ ጋምቤላ ይገኙበታል (ምስል 1)፡፡ በተጨማሪም ከክረምት ወቅት ጀምሮ ዝናብ ሲያገኙ የነበሩት የደቡብ ምዕራብ እና የምዕራብ የሀገሪቱ አከባቢዎች ከቀላል እስከ መካከለኛ መጥን ያለዉ አግኝተዋል፡፡ በሌላ በኩል በሰሜን ምዕራብ፣ ምዕራብ እና ሰሜን የሀገሪቱ አከባቢዎች በጥቂት ቦታዎቻቸዉ ላይ አልፎ አልፎ በነበሩት ቀናት ወቅቱን ያልጠበቀ አነስተኛ መጠን ያለዉ ዝናብ ተመዝግቧል (ካርታ 1 )፡፡





ምስል፥1 ከኦክቶበር 1-31 በ24 ሰዓት ውስጥ ከ50 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ የተመዘገበባቸው

ባለፈዉ ወር በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸዉ በሆኑት አከባቢዎች የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም፤ ከኦሮሚያ ክልል የቦረና፣ የምስራቅ ቦረና፣ የጉጂ እና ምዕራብ ጉጂ ዞኖች፣ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል የጋሞ፣ ባስኬቶ፣ አሪ፣ ኮንሶ፣ ቡርጂ፣ አሌ፣ ጋርዱላ፣ ኮሬ እና ደቡብ ኦሞ ዞኖች፣ ከሱማሌ ዳዋ፣ ሊበን፣ አፍዴር እና ቆራሂ ዞኖች ላይ ከ61-500 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ ከ5-28 ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸዉ (ካርታ 1 እና 2)፡፡ በተመሳሳይ ቀደም ብሎ የክረምት ወቅት ዝናብ እያገኙ የነበሩት ከኦሮሚያ ክልል የቄለም ወለጋ፣ ምዕራብ ወለጋ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ሆሮ ጉድሩ ወለጋ፣ ኢሉባቦር፣ ቡኖ በደሌ፣ ጅማ ዞኖች፤ ከአማራ ክልል ምዕራብ ጎንደር፣ የአዊ፣ የባህርዳር ዙሪያ ዞኖች፣ ከጋምቤላ ክልል አኝዋክ፣ መዥንግ፣ የኑዌር እና የኢታንግ ልዩ ወረዳ፤ ከቤንሻንጉል ጉምዝ ካማሺ፣ መተከል፣ አሶሳ፣ ማኦ ኮሞ ዞኖች፣ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ኮንታ፣ ዳዉሮ፣ ከፋ፣ ሸካ፣ ቤንች ሸኮ ዞኖች ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል የጎፋ፣ የወላይታ እና ጌዲዮ ዞኖች፣ የሲዳማ ክልል ዞኖች ላይ ከ61-713 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ ከ9-28 ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸዉ (ካርታ 1 እና 2)፡፡


በሌላ በኩል የሰሜን፣ መከከለኛዉና ደቡብ ጎንደር፣ የምዕራብና የምስራቅ ጎጃም ዞኖች፣ ከትግራይ ክልል የምዕራብ፣ ሰሜን ምዕራብና ደቡብ ትግራይ ዞኖች፤ ምስራቅ ባሌ፣ ባሌ፣ አርሲ እና ምዕራብ አርሲ ዞኖች፣ ምዕራብ ሐረርጌ፣ አዲስ አበባ እና ሐረሪ፣ ከማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ጉራጌ፣ ሃዲያ፣ ስልጤ፣ ከንባታ፣ የሃላባ፣ የም፣ ቀቤና ዞኖች ላይ ወቅቱን ያልጠበቀ ከ 21-100 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ ከ2-4 ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸዉ (ካርታ 1 እና 2) ፡፡

ባለፈዉ ወር የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸዉ ከሆኑት የሀገሪቱ አከባቢዎች ከኦሮሚያ ክልል የቦረና፣ የምስራቅ ቦረና፣ የጉጂ እና ምዕራብ ጉጂ ዞኖች፣ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል የጋሞ፣ ባስኬቶ፣ አሪ፣ ኮንሶ፣ ቡርጂ፣ አሌ፣ ጋርዱላ፣ ኮሬ እና ደቡብ ኦሞ ዞኖች፣ ከሱማሌ ዳዋ፣ ሊበን፣ አፍዴር፣ ሸበሌ፣ ቆራሂ፣ ዶሎ ዞኖች ላይ በአብዛኛዉ መደበኛና ከመደበኛው በላይ የሆነ የዝናብ መጠን ተመዝግቧል (ካርታ 3) ፡፡


በሌላ በኩል በመጨረሻዎቹ አስራ አንድ ቀናት በመካከለኛዉ፣ በሰሜን ምሥራቅ እና የደቡብ ደጋማ ቦታዎች ላይ የለሊቱና የማለዳው ቅዝቃዜ አልፎ አልፎ በነበሩት ቀናት የተስተዋለ ሲሆን፤ ደበረ ብርሃን፣ ሐሮማያ፣ አለም ከተማ፣ በሂ፣ ጅግጅጋ፣ ሾላ ገበያ፣ አምባ ማሪያም፣ ወገል ጤና የቀኑ ዝቅተኛ የሙቀት መጠን ከአምስት (5) ዲግሪ ሴልሺየስ በታች ተመዝገቧል፡፡




ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ 31/2025 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ




ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ 31/2025 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸዉ ቀናት





ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ 31/2025 የነበረዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር

Ethiopian Meteorology Institute

## 1.2 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ 31/2025 የነበረው የአየር ጠባይ በግብርና ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባሳለፍነው የኦክቶበር ወር የነበረው የእርጥበት ሁኔታ በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት በደቡብና ደቡብ ምስራቅ የሀገራችን አካባቢዎች በተለይም በቦረና፣ ጉጂ እና የደቡብ ክልል ደቡባዊ ዞኖች  ለሚካሄደው የሰብል ልማት የማሳ ዝግጅት ለማድረግና  ዘር ለመዝራት ምቹ ሁኔታ ፈጥሯል፡፡ በተጨማሪም በደቡብ ምዕራብና ምዕራብ አጋማሽ በሚገኙ የሀገራችን አካባቢዎች ተጨማሪ እርጥበት ለሚያስፈልጋቸው እና ፍሬ በመሙላት ላይ ለሚገኙ የመኸር ሰብሎች የውሃ ፍላጎታቸውን ከማሟላት አንጻር ከፍተኛ ጠቀሜታ ነበረው፡፡ በመሆኑም በዚህ ወቅት የተገኘው እርጥበት በተለይም ለአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች የግጦሽ ሳርና የመጠጥ

ውሃ አቅርቦትን ከማሻሻል አንጻር ከፍተኛ ጠቀሜታ ነበረው፡፡ በሌላ በኩል በሰሜን፣ በሰሜን ምዕራብ፣ በሰሜን ምስራቅ፣ በምስራቅና በመካከለኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የነበረው እርጥበት ዘግይተው ተዘርተው ዕድገታቸውን ላልጨረሱና ከመስከረም ወር መጀመሪያ ጀምሮ በአፈር ውስጥ በሚገኝ እርጥበት ለተዘሩ እንደ ሽንብራና ጓያ ላሉ የጥራጥሬ ሰብሎች፣ ለቋሚ ተክሎች፣ ለጓሮ አትክልቶችና ለፍራፍሬዎች የውሃ ፍላጎታቸውን ከማሟላት አንጻር አዎንታዊ ጎን ነበረው፡፡ በሌላ በኩል በሰሜን፣ በሰሜን ምዕራብ፣ በሰሜን ምስራቅና በምስራቅ እንዲሁም በአንዳንድ የመካከለኛው የሀገራችን አካባቢዎች የነበረው ደረቅ ሁኔታ ቀደም ብለዉ ለደረሱ የመኸር ሰብል ስብሰባና ድህረ ሰብል ስብሰባ የጎላ ጠቀሜታ ነበረው (ካርታ 4) ፡፡





ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ 31/2025 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ

## 1.3 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ 31/2025 የነበረው የአየር ጠባይ በውሃው ዘርፍ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባሳለፍነው ኦክቶበር ወር የነበረው የአየር ሁኔታ በአብዛኛው ባሮ አኮቦ፣ ኦሞጊቤ፣ ገናሌ ዳዋ፣ ኦጋዴን ስምጥ ሸለቆ፣ ዋቤ ሸበሌ፣ በመካከለኛው እና በታችኛው ተከዜ እንዲሁም በጥቂት አፋር ደናክል ተፋሰሶች ላይ ከእርጥበታማ እስከ ከፍተኛ የሆነ የገፀ ምድር የውሃ ፍሰት ነበራቸው፡፡ በተጨማሪም በታችኛው አባይ፣ በላይኛው እና በመካከለኛው ባሮ አኮቦ በታችኛው ኦሞ ጊቤ እና በጥቂት ላይኛው ገናሌ ዳዋ ተፋሰሶች ላይ በጣም ከፍተኛ የገፀ ምድር የውሃ ፍሰት ነበራቸው፡፡ ይህ ወቅታቸው ለሆኑ ግድቦች እና ለሌሎች ውሃ መያዣዎች ጥሩ ገብዓት እንደነበረው የተተነተኑ የውሃ ሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች ያሳያሉ፡

፡ በሌላ በኩል በአብዛኛው አዋሽ፣ አፋር ደናክል፣ በላይኛው ተከዜ፣ በላይኛው መስራቃዊ አባይ ተፋሰሶች ላይ ደረቅ ሁኔታ ስር ነበሩ (ካርታ 5) ።




ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ 31/2025
ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ

Ethiopian Meteorology Institute

# በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣ ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ

## 1. መግቢያ


የበጋ ወቅት ከኦክቶበር እስከ ጃንዋሪ ያሉትን ወራት የሚያካትት ሲሆን፤ ለደቡብና ደቡብ ምሥራቅ የሀገሪቱ አከባቢዎች ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው ነው፡፡ የበጋ ወቅት ከዓመታዊ የዝናብ መጠኑ እስከ 45% የሚደረሰውን የሚሸፍን ሲሆን ከበልግ ቀጥሎ የተሻለ ዝናብ የሚኖርበት ወቅት ነው። በኖቬምበር ወር የበጋው ዝናብ በአብዛኛዉ በደቡብና ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ላይ የሚወሰን በመሆኑ የደቡብ ኦሮሚያ፤ የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ዞኖች፤ የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ዞኖች፤ የሲዳማ ዞኖች ከ5-10 ቀናት ዝናብ የሚኖራቸው ሲሆን በመጠን ከ 50-100 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ ያገኛሉ። በተጨማሪም የሶማሌ ደቡባዊ ክፍል ከ5-10 ቀናት ዝናብ የሚያገኝ ሲሆን፣ የተቀሩት የሰሜን ምሥራቅ እና የምዕራብ ቆላማ አካባቢዎች ከ2 ለማይበልጡ ቀናት አነስተኛ ዝናብ የሚያገኙ ሲሆን፤ በመጠን 3-25 ሚ.ሜ ዝናብ ያገኛሉ።

### 1.1 እ.ኤ.አ ከኖቬበር 1 እስከ 30/2025 የሚኖረው የአየር ጠባይ

በመደበኛ ሁኔታ በኖቬምበር ወር በአብዛኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የበጋው ደረቅ ፀሐያማና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ ከማመዘኑ ጋር ተያይዞ በአንዳንድ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ የሌሊቱና የማለዳው ቅዝቃዜ የሚስተዋልበት ወር ነው፡፡ በሌላ በኩል በደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ዝናቡ እስከ ወሩ አጋማሽ ድረስ ቀጣይነት ይኖረዋል፡፡

በሚቀጥለው የኖቬምበር ወር ዝናብ ሰጪ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች እስከ ወሩ አጋማሽ ደረስ ቀጣይነት እንደሚኖራቸዉና ከሚጠናከሩት የአየር ሁኔታ ክስተቶች በመነሳት በተለይም በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት የቦረና የምስራቅ ቦረና፣ የምዕራብ ጉጂ እና ጉጂ ዞኖች፤ የሲዳማ ክልል ዞኖች፤ የሶማሌ ክልል ደቡባዊና ደቡብ ምስራቅ ዞኖች እና የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ደቡባዊ ዞኖች ላይ ቀጣይነት ያለው ዝናብ እንደሚኖራቸው አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ (ካርታ 6)፡፡ በተጨማሪም ቀደም ብሎ የክረምት ወቅት ዝናብ እያገኙ የነበሩት የደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ አስከ ወሩ አጋማሽ ድረስ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለዉ ያለው ዝናብ እንደሚኖራቸዉ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ በሌላ በኩል  በጸሀይ ኃይል ታግዘው ከሚጠናከሩት የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ላይ በመነሳት በምስራቅ፣ በሰሜን ምስራቅ እና በሰሜን ምዕራብ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ ከሚጠናከሩት የአየር ሁኔታ ክስተቶች ላይ በመነሳት ወቅቱን ያልጠበቀ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለዉ ዝናብ ይኖራል (ካርታ 6)፡፡ በተጨማሪም በመካከለኛዉ፣ በሰሜን ምሥራቅ እና የደቡብ

ደጋማ ቦታዎች ላይ የለሊቱና የማለዳው ቅዝቃዜ አልፎ አልፎ በሚኖሩት ቀናት ከአምስት (5) ዲግሪ ሴልሺየስ በታች እንደሚሆን የትንበያ መረጃዎች ያሳያሉ። ስለሆነም በሚኖሩት ደረቅ ቀናቶች የደረሱ ሰብሎች መሰብሰብ አስፈላጊ መሆኑን የኢትዮጵያ ሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት ይጠቁማል፡፡




ካርታ 6 እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 1-30፣ 2025 የሚኖረው የዝናብ ሁኔታ ከረጅም ጊዜ አማካይ ጋር ሲነፃጸር

## 1.2 እ.ኤ.አ ከኖቬበር 1 እስከ 30/2025 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥለው የኖቬምበር ወር በተለይም የመኸር ሰብል አብቃይ በሆኑት የደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ እስከ ወሩ አጋማሽ ሊኖር የሚችለው እርጥበት በተለያየ ምክንያት ዘግይተው ለተዘሩና የእድገት ጊዜያቸውን ላልጨረሱ የመኸር ሰብሎች፣ ለቋሚ ተክሎችና ፍርፍሬዎች የውኃ ፍላጎት መሟላት ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል። በተጨማሪም በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት የቦረና፣ ምስራቅ ቦረና፣ ምዕራብ ጉጂ፤ ጉጂ፤ ሲዳማ ክልል ዞኖች፣ የሶማሌ ክልል ደቡባዊና ደቡብ ምስራቅ ዞኖች እና የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ደቡባዊ ዞኖች የሚጠበቀው እርጥበት ለአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች ለእንስሳት መኖና የመጠጥ ውሃ አቅርቦት መሻሻል ከፍተኛ ጠቀሜታ ከመኖሩም በተጨማሪ በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወታቸው በሆኑት አካባቢዎችና የበጋ ሰብል በሚያመርቱ እንደ ቦረናና ጉጂ ለመሳሰሉ አካባቢዎች ለሚኖረው የግብርና ስራ እንቅስቃሴ የጎላ ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡ በአጠቃላይ

በዚህ ወር የሚገኘው እርጥበት በተለይም ውሃ አጠር በሆኑ አካባቢዎች የሚገኘውን የዝናብ ውሃ ለመሰብሰብና ለማከማቸት መልካም አጋጣሚን የሚፈጥር ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ማህበረሰቡ እና የሚመለከታቸው አካላት ይህንን ለማከናወን የሚያስችል ቅድመ ዝግጅት ማድረግ ያስፈልጋል። በአንጻሩ ግን የመኸር ሰብል አብቃይ በሆኑ በምስራቅ፣ ሰሜን ምስራቅ እና ሰሜን ምዕራብ የሀገራችን አካባቢዎች ሊኖር የሚችለው ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለዉ ወቅቱን ያልጠበቀ ዝናብ በተለይም በደረሱ እና በመሰብሰብ ላይ በሚገኙ እንደ ሰሊጥ፣ ጤፍ፣ ገብስ፣ አጃ እና ስንዴ እንዲሁም ቀድመው በሚደርሱ እንደ በቆሎ እና ማሽላ የመሳሰሉት የረጅም ጊዜ ሰብሎች ላይ አሉታዊ ጎን ሊኖረው ስለሚችል አርሶ አደሮች እና የሚመለከታቸው አካላት በየጣልቃው የሚኖረውን ደረቅ ቀናቶች በመጠቀም የደረሱ ሰብሎችን በወቅቱ መሰብሰብ ያስፈልጋል። በተጨማሪም አልፎ አልፎ በመካከለኛዉ፣ ሰሜን ምሥራቅ እና ደቡብ ደጋማ ቦታዎች ላይ የለሊቱና የማለዳው ቅዝቃዜ ክስተት በሚጠበቅባቸው የሀገሪቱ አካባቢዎች በሰብሎችና በመስኖ በሚበቅሉ አዝዕርቶች ላይ ጉዳት እንዳይደርስ ቅድመ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

## 1.3 እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 1 እስከ 30/2025 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ በዉሀዉ ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥለው የኖቬምበር ወር በአብዛኛው ባሮ አኮቦ፣ ኦሞ ጊቤ፣ ገናሌ ዳዋ፣ ኦጋዴን በመካከለኛው እና በታችኛው ስምጥ ሸለቆ፣ ዋቢ ሸበሌ የተሻለ የገፀ ምድር ውሃ ፍሰት ይኖራቸዋል፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ የሚገኘውን የዝናብ ውሃ የተለያዩ የውሃ መሰባሰብያ ዘዴዎች በመጠቀም በተለይም ውሃ አጠር በሆኑ ተፋሰሶች ላይ ለቀጣይ ደረቅ ወቅት የውሃ እጥረት መቀነስ ያስፈልጋል፡፡ በሌላ በኩል በአብዛኛው አፋር ደናክል፣ አዋሽ፣ ተከዜ፣ መረብ ጋሽ እንዲሁም አይሻ ተፋሰሶች ላይ ደረቅ የአየር ጠባይ ተጽዕኖ ስር ይቆያሉ።